


# “ ድንቅ ስራውን መስክሩ “



በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ አምላክ አሜን !

ከሁሉ በፊት ተበታትነን እንዳንቀር ለአሰባሰበን ሳንፈልገው ለፈለገን በደለኞች ሁነን ሳለ በደላችንን ላልቆጠረብን በአንድ ላይ ሁነን ስሙን እንድናመሰግን ለፈቀደልን አነሳስቶ ለአስጀመረንና ለአስፈፀመን ለፍቅር አምላክ ለልዑል እግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይድረሰው አሜን !

## በኦታዋ የቅዱስ ተክለሃይማኖት ቤተ ክርስትያን አመሰራረትና እድገት

ቤተ ክርስትያኑ እንዴት ተመሰረተ ለምስረታው መክንያት የሆነው ምንድን ነው ?አላማውስ ምን ነበር ?

አንዳንድ እህቶችና ወንድሞች የቀደ እምነታቸውን በመተው የአዲስ እምነት ተከታዮች ሲሆኑ ሌሎች ደግሞ በጭንቀት እራሳቸውን ሲጎዱና ሲባዝኑ ሁኔታው ያሳሰባቸውና ያሳዘናቸው ወንድሞች ይህ ጥፋት ሊገታ የሚችለው ምን ቢደረግ ነው በማለት ጥናት ጀመሩ ። በመጨረሻ ምወገኖችን በቤተክርስትያን ማሰባሰብና ማገናኘት የችግሩ መፍትሄ እንደሚሆን ተገነዘቡ ።

ቤተክርስትያኑ የተመሰረተበት አላማ ከአገር ፣ ከወንዝ ፣ ከቤተሰብ ፣ ከለመዱት ባህልና ከቀደመ እምነታቸው ተለይተው ብቸኛ በመሆን በጭንቀት ላይ የወደቁትን ወገኖች በቤተክርስትያን አሰባስቦ ቅዱስ ወንጌልን በማስተማር ከዚህ ችግራቸው ነፃ እንዲሆኑ ፣የአዲስ እምነት ተከታዮች የሆኑትም ወገኖች ወደ ቀደመ እምነታቸው እንዲመለሱ ለማድረግ ነበር።

ይህን አላማ በተግባር ለመተግበ የእግዚአብሔር ፍቃዱ ሲደርስ ሚያዝያ ፳ ቀን ፲፱፻፹፩ ዓ.ም ሶስት ሰዎች ሆነው በአቶ አቻምየለህ ገሠሠ ቤት ተሰብስበው በጥናታቸው መሰረት ለሚያውቋቸው ሁሉ በስልክ እየጠሩ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስትያን ልንመሰርት ነውና በሃሳቡ ትስማማላችሁ በማለት መጠየቅ አደረጉ ። የተጠሩትም አዎንታ መልስ በመስጠት ፍቃደኝነታቸውን ገለፁ። ስለሁኔታው ለመወያየት በሚያዚያ ፲፮ ቀን ፲፱፻፹፩ ዓ.ም ፈቃደኛ ለሆኑት ስብሰባ በሚጠራበት ጊዜ አቶ ሞገስ ዋሴ የተባለ ወንድም ስብሰባው በእርሱ ቤት እንዲደረግ ስለፈቀደ በዚሁ ወንድም ቤት እነዲገኙ መምጣት ለሚፈልጉ ሁሉ ተነገረ ። በጉጉት ይጠበቅ የነበረው ሚያዚያ፲፮ ቀን ፲፱፻፹፩ ዓ.ም ደርሶ በተባለው ቦታ ለስብሰባው የተገኙት ስብሰባውን የጠሩት ዶ/ር ደሰታ ውቤ ፣ አቶ መሐሪ አለሙ ፣ አቶ አቻምየለህ ገሠሠ እንዲሁም ቤቱን ለስብሰባ የፈቀደው አቶ ሞገስ ዋሴና አቶ አዱኛ ውቤ የሚባል ወንድም ሲሆን በጠቅላላው በስብሰባው ላይ የተገኙት አምስት ሰዎች ነበሩ ።እነሱም ይህ ቀን ቤተ ክርስትያን ተመስርቷል ተብሎ ለሚመለከታቸው ሁሉ በይፋ የተነገረበት ስለሆነ ቤተክርስትያኑ የተመሰረተበት ቀን ተብሎ እንዲጠራ በዚሁ ዕለት ተወሰነ ።

በሚያዚያ ሉ3 ቀን ለ9ሚመ5 ዓ.ም ለሁለተኛ ጊዜ በዚሁ ወንድም ቤት በተደረገው ስብሰባ አስር ሰዎች ተገኝተው ቅንጅት ያለው ስራ ለመስራት ያመች ዘንድ የመጀመርያውን የቦርድ አባላት መረጡ። ሚያዚያ ሊ ቀን ለ9ሚመ5 ዓ.ም እና ግንቦት ለ ቀን ለ9ሚመ5 ዓ.ም በኢትዮጵያዊያን ማህበር ጽ/ቤት ከተሰበሰቡ በኋላ 82 ኬንት ስትሪት የሚገኘው ሴንት አንድሪ ፕሪስቤትርያን ቤተክርስትያን በሳምንት አንድ ቀን የምንፀልይበት አንድ ክፍል ሰለሰጡን በግለሰቦች ቤትም ሆነ በኢትዮጵያዊያን ማህበር ጽ/ቤት ይደረግ የነበረው ስብሰባ ግንቦት ለቀን ለ9ሚመ5 ዓ.ም የመጨረሻ ቀን ሆነ። ቤተክርስትያኑ ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ እስከዚህ ቀን ድረስ ውይይት እንጅ ትምህርት አይሰጥም ነበረ።

ግንቦት ፲፪ ቀን ፲፱፻፹፭ ዓ.ም በዚሁ በተሰጠን ሴንት አንድሪ ፕሪስቤትርያን ቤተ ክርስትያን ትንሽ ክፍል ውስጥ ለመጀመርያ ጊዜ በዶ/ር ደስታ ለምዕመናን የመፅሐፍ ቅዱስ ትምህርት ተሰጠ ። በዚሁ ዕለት ሁለት እህቶች የቦርድ አባል ሆነው ሲመረጡ ስምንት ሰዎች ደግሞ መዘምራን ለመሆን ተመዘገቡ ። ግንቦት ፳፱ ቀን ፲፱፻፹፭ ዓ.ም ወ/ሪት እመቤት ሽፈራው ፣ ወ/ሪት መዓዛ ካህሳይና አቶ በላይ ግርማይ ለመጀመርያ ጊዜ በምዕመናን ፊት ወጥተው በመዘመር ሌሎች መዘምራን ፍራትን በመተው እንዲዘምሩ መልካም አርአያ በመሆን አሁን ለአለውና እዚህ ለደረሰው የቤተ ክርስትያኑ መዘምራን የእድገት በር ከፍተዋል ። ሰኔ ፲፭ ቀን ፲፱፻፹፭ ዓ.ም የቤተክርስትያኑን መተዳደርያ ደንብ አርቅቀው ረቂቁን ለሰበካ ገባዔው የሚያቀርቡ ሶስት ሰዎች ተመረጡ ። የተመረጡትም ሰዎች እረቂቁን ሰኔ ፲፰ቀን ፲፱፻፹፭ ዓ.ም ለሰበካ ጉባዔው አቀረቡ። ሰበካ ጉባዔውም መስተካከል የሚገባቸውን አስተካክሎ ሰኔ ፲፱ ቀን ፲፱፻፹፭ ዓ.ም የቤተ ክርስትያኑን ደንብ አፀደቀ ። ወዲያውኑ በካናዳ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን ኦታዋ በሚል ስም ፈቃድ እንዲሰጠን የሚጠይቀውን ማመልከቻና የቤተክርስትያኑን መተደዳርያ ደንብ ለሳይንስና እንድስትሪ ሚንስትር ተላከ። መስርያ ቤቱም በዚህ ቤተክርስትያን ስም የሚጠራ ቶሮንቶ ስለአለ ከዚህ ቤተክርስትያን ስጧቸው የሚል የፈቃድ ደብዳቤ ካላመጣችሁ ፈቃድ አይሰጣችሁም ብሎ ፃፈ።

መስከረም ፲፩ ቀን ፲፱፻፹፭ ዓ.ም ለቶሮንቶ ቅድስት ማርያም ካቴድራል አስተዳዳሪ ለሊቀ ካህናት ምሳሌ እንግዳ ሁኔታውን በዝርዝር የሚገልጽ ማመልከቻና መተዳደርያ ደንቡ ተላከላቸው። ሊቀ ካህናትም በሁኔታው በጣም ተደስተው ኑና ተመካክረን ፈቃዱን ትወስዳላችሁ በማለት ፈቃደኛ መሆናቸውን ገለጹ። ሁለት ሰዎች ወደ ቶሮንቶ ተልከው ከሊቀካህናት ምሳሌና ከቤተክርስትያኑ ጠበቃ ጋር ከተወያዩ በኋላ እንዲሰሩ ፈቅደንላቸውል የሚል ደብዳቤ ይዘው መጡ። የመጣው ደብዳቤ ለሳይንስና እንድስትሪ ሚንስትር ተሰጠ።ሕዳር ፲፱፻፹፮ ዓ.ም በካናዳ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን ኦታዋ ተብሎ እንዲጠራ ፍቃድ ተገኘ።

በቤተ ክርስትያናችን ሥርዓት መሰረት ያለታቦት ስያሜ ቤተ ክርስትያን ስለማይጠራ ቤተክርስትያኑ ሕጋዊ አካሉን እንዳገኘ ቤተ ክርስትያኑን በማንኛው ታቦት ስም ይጠራ የሚል ውይይት ሰበካ ጉባዔውና ምዕመኑ አካሄዱ። ከፊሉ የታቦቶች ስም ዝርዝር ይፃፍና ለድምፅ ይቅረቡ የድምፅ ብልጫ ያገኘው ታቦት የቤተክርስትያኑን መጠርያ ይሁን ሲል ሌላውክፍል ደግሞ የሁሉም ታቦት ስም ዝርዝር ይፃፍና እጣ ይጣል እጣው የወጣለት ታቦት የቤተ ክርስትያኑ መጠርያ ይሁን የሚል ሃሳብ ቀረበ። የሁለተኛውን ሃሳብ ሁሉም ስለተቀበለው የሁሉም ታቦቶች ስም ተፅፎ እጣው ተጠቅልሎ መጋጠምያ ባላት ሙዳይ ተቀምጦ ሁለት ሳምንት እንዲፀለይበትና እግዚአብሔር የፈቀደው እንዲወጣ ተደረገ። ከሁለት ሳምንት ፀሎት በኋላ እጣው ከመውጣቱ በፊት ሆሉም ምዕመናን ለአምስት ደቂቃ ተንበርክኮ እንዲፀልይ ተደረገ። ከፀሎቱ በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ በሕፃን ኢዛና ኪሮስ እጅ ተክለሃይማኖት የሚለው ታቦት ስም የዕጣው አሸናፊ በመሆን ወጣ ። ከዚህ ቀን ጀምሮ በካናዳ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን ኦታዋ ተብሎ ተሰየመ። ወድያውኑ በዚህ ቤተክርስትያን ስም የባንክ ሂሳብ ተከፍቶ የሂሳቡ ቁጥር ለምዕመናንና ቤተ ክርስትያኑን ለመርዳት ፍላጎት ለአላቸው ሁሉ ይፋ ተደረገ።

## ካህናት

ካህን የሌለው ቤተክርስትያን ተፈላጊውን አገልግሎት ለምዕመናን ስለማይሰጥና ሥርዓትም ስለማይኖረው የካህን መኖር ግዴታ ስለነበር ካህን እንዲመጣ ተወስኖ ካህን በመፈለግ ላይ እንዳለ የካቲት ፫ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ.ም አባታችን አቡነ መልከጼዴቅ ሊጠይቁን በመጡ ጊዜ ጊዜአዊ ካህን በቅርቡ እንደሚልኩልን ቃል ገብተውልን ተመለሱ ። አባታችንም በገቡት ቃል መሰረት ሚያዝያ ፰ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ.ም አባ መሪጌታ ሲራክ ሉሌን ላኩልን ።አባ መሪ ጌታ ሲራክም የኦታዋ ቅዱስ ተክለ ሃይማኖት ቤተክርስትያን የመጀመርያው ካህን ነበሩ ። አባ መሪ ጌታ ሲራክ ጊዛዊውን ችግር ብቻሳይሆን ቋሚ ካህን የሚገኝበትን መንገድ በመፈልግ የምዕራብ አገሮች ሊቀ ጳጳስ አቡነ ይስሃቅን ከኒውዮርክ በማስመጣት ሐምሌ ፳፱ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ.ም በግብፅ ኮፕቲክ ገዳም መርጌታ ምስራቅ ኃይሉን አባ ገብረ እግዚአብሔር በማለት የቅስናና የምንኩስና ማዕረግ ፣ የዚህ ቤተክርስትያን መስራች የሆኑትን ዶ/ር ደስታ ውቤን አባ ገብረ ማርያም በማለት የቅስናና የምንኩስና ማዕረግ፣ወንድም ዮሴፍ ኃይሉን የዲቁና ማዕረግ እንዲሰጣቸው በማድረግ መፍትሄ አጥቶ የነበረውን ችግር አቃለዋል ። በተጨማሪም ከሰበካ ጉባዔው ጋር በመተማባበር ንዋየ ቅድሳቱን አሟልተው ወደ ቀድሞ ቦታቸው ተመለሱ።

እነዚህ ሁለት አባቶችና አንድ ዲያቆን ባንድ ሆነው ለተወሰነ ጊዜ ካገለገሉ በኋላ አባ ገብረ ማርያም ወደ አሜርካ ሄዱ። አባ ገብረ እግዚአብሔርና ዲያቆን ዮሴፍ ኃይሉ በማገልገል ላይ እንዳሉ አባ ገብረ እግዚአብሔር ድንገት ታመው ታህሳስ ፳፩ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም በሞት ተለዩ። ቤተክርስቲያኑም ያለ ካህን ቀረ ለቤተ ክርስትያናችን ዕድገት እንቅፋት የሆነው ችግር አሁንም ተደገመ። ብዙ ችግሮች ተፈራረቁብን ። ቤተክርስትያኑ ሲመሰረት ጀምሮ ከጎናችን ያልተለዩን የቶሮንቶ ቅድስት ማርያም ካቴድራል አስተዳዳሪ ሊቀ ካህናት ምሳሌ እንግዳ ሁለተኛ ካህን ሆነው ያገለግሉ የነበሩትን አባ ሳሙኤል ተሻገርን ላኩልን። አባ ሳሙኤልም አንድ አመት አገልግለው ሄዱ። አሁንም ለስምንት ወር ያለ ካለህን ከቆየን በኋላ በቶሮንቶ ቅድስት ማርያም አባቶች ትብብር የእግዚአብሔር ፈቃዱ ሆኖ ጥቅምት ፲፯ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም አባታችን አባ ኃይለ ገብረኤል ወንድሙ ካሴ በቋሚነት መጡልን። ለቤተክርስትያናችን ዕድገት ጎታች የነበረው ችግር ተወገደ።

ዲያቆን ዘካርያስ ሀብተወልድ ፣ ዲያቆን ዮሴፍ ኃይሉ፣ ዲያቆን ሳምሶን አምባዬና ዲያቆን መላኩ ሀብተሃና አባቶች ሲኖሩ ከአባቶች ጋር አባቶች በሌሉ ጊዜ የአባቶችን ቦታ በመተካት ኪዳን በማድረስ ቅዱስ ወንጌል በማስተማርና ምዕመናንን በማፅናናት ቤተክርስትያናችን ከዚህ ደረጃ እንዲደርስ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያበረከቱ የቅዱስ ተክለሃይማኖት የበረከት ልጆች ናቸው።

## የልማትና ሕንፃ ኮሚቴ

ቤተክርስትያኑ እያደገና የምዕመናን ቁጥር እየጨመረ ስለሄደ ምዕመናንም የአባልነት ክፍያ መክፈል ስለጀመሩ የራሳችን የሆነ ሕንፃ ቤተክርስትያን መኖሩ ስለታመነና መግዛት አስፈላጊ በመሆኑ ይህን እቅድ ለመተግበር ሁኔታዎችን የሚያመቻች የልማትና ሕንፃ ኮሚቴ መስከረም ፲፱፻፺፫ ዓ.ም በአቶ አበበ እንግዳሰው ፣አቶ ኬና አንተንሳይና ፣አቶ ኒሻን ሃይለ መስቀል ተቋቋመ። ኮሚቴው ወድያውኑ ስራ በመጀመር የአጭርና የረጅም ጊዜ ዕቅዶችን ነደፈ።

የአጭር ጊዜ ዕቅዱ ቤተክርስትያኑ በተለያየ መልኩ የሚጠናከርበትን መንገድ በመተለም ጥናቱን ለሰበካ ጉባዔው ማቅረብ ሲሆን የረጅም ጊዜ ዕቅዱ ቤተክርስትያኑ የራሱ የሆነ ሕንፃ እንዲኖረው ማድረግ ነበር።

ኮሚቴው በዕቅዱ መሰረት ከሰበካ ጉባዔው ጋር በመተባበር ሚያዚያ ፲፱፻፺፫ ዓ.ም ለመጀመርያ ጊዜ ሕንፃ ቤተ ክርስትያን ለመግዛት የሚያስችል የገንዘብ ዕቅድ አወጣ። ዕቅዱም በአምስት አመት ተከፍሎ በሚያልቅ Cd$350,000 ሕንፃ ቤተ ክርስትያን ብንገዛ እያንዳንዱ ምዕመን በቀን Cd$1.00 በዓመት Cd$365.00 በአምስት አመት Cd$1,825.00 ቢከፍል በአጭር ጊዜ ውስጥ የሕንፃ ቤተ ክርስትያን ባለቤቶች እንሆናለን የሚል ነበር። ዕቅዱም ተቀባይነት አግኝቶ ምዕመናን ገንዘቡን በመክፈል ላይ እንዳሉ መጋቢት 15 ቀን 1994 ዓ.ም ሌላ ተጨማሪ የገንዘብ ዕቅድ ተዘረጋ። ይህም ዕቅድ ዕመናን ይከፍሉት የነበረው$ 10.00 ና $15 ወርሃዊ ክፍያ ወደ Cd$20.00 ና Cd$30.00 ከፍ ቢል የቤተክርስትያኑ ገቢ አስተማማኝ ስለሚሆን ብዙ ወለድ ሳንከፍል ሕንፃ ቤተ ክርስትያን መግዛት እንችላለን የሚል ነበር። ይህም ዕቅድ ተቀባይነት አግኝቶ የተባለው ወራዊ ክፍያ ገቢራዊ ሆኖ እስካሁን ምዕመናን በመክፈል ላይ ናቸው።

ይህ የልማትና ሕንፃ ኮሚቴ በረጅም ጊዜ ዕቅዱ መሰረት ከሰበካ ጉባዔው ጋር በመተባበር ሕንፃ ቤተክርስትያን ሊሰራባቸው የሚችል የተለያዩቦታዎችንና ሕንፃዎችን ለመግዛት ከተለያዩ አብያተ ክርስትያኖችና ድርጅቶች ጋር በመነጋገርና በመደራዳር ብዙ ውጣ ወረዶችን ከአሳለፈ በኋላ የልዑል እግዚአብሔር ፍቃድ ሲደርስ 915 ሜርቨል ሮድ ላይ ለሚገኘው ሕንፃ ቤተክርስትያን ባለቤቶች እንድንሆን ከፍተኛውን ሚና ተጫውቷል።

## መዘምራን

የኦታዋ ቅዱስ ተክለ ሃይማኖት መዘምራን ከተቋቋመበት ከግንቦት ፲፪ ቀን ፲፱፻፹፭ ዓ.ም ጀምሮ በዝማሬ እግዚአብሔርን ከማገልገላቸው በላይ ከምእመና ጋር በመተባበር ቤተ ክርስትያኑ ገቢ የሚ

ያገኙበትን መንገድ በመቀየስ የተለያዩ ዝግጅቶችን በማዘጋጀት ምግብና እቃዎችን በመሸጥ እና የመሳሰሉትን በማድረግ የቤተ ክርስትያኑ ገቢ እንዲዳብር ያደረጉ ችግሮችና ፈተናዎች በተፈራረቁብን ጊዜ ምእመናን በማጽናናት ከአገልግሎታቸው ገለል ሳይሉ ሁሉን በትዕግስት እየተወጡ ቤተ ክርስትያናችንከዚህ ደረጃ እንዲደርስ ከፍተኛ ድርሻ ያበረከቱ መንፈስ ጠንካሮች የተክልዬ ልጆች ናቸው።

## ምዕመናን

የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ የነበሩት የጥንት አባቶችና እናቶች ምዕመናን ከሐይማኖት አባቶች ጎን በመቆም የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን ሥርዓቷንና ሕጓን በማክበር ሕንፃ ቤተክርስትያን በማነፅ አሁን ለአለንው ትውልድ አስረክበውን አልፈዋል። የኦታዋ ቅዱስ ተክለ ሃይማኖት ቤተክርስትያን ምዕመናን በቁጥራቸው አነስተኛ ቢሆኑም ከቀደሙ አባቶችና እናቶች በተረከቡት እምነታቸው ጸንተው የቤተክርስትያናቸውን አነድነት ጠብቀው በፍቅርና በመተሳሰብ ጉልበታቸውን ፣ እውቀታቸውንና ገንዘባቸውን አስተባብረው ተግተው በመስራት በልዑል እግዚአብሔር እርዳታና ፍቃድ የሕንፃ ቤተክርስትያን ባለቤቶች ለመሆን የበቁ የእምነት አርበኞች ናቸው ። ቤተክርስትያናችን ከተመሰረተአስራ አንድ አመት ሲሆነው በነዚህ አመታት ውስጥ የተከፈለው መስዋዕት እጅግ ውስብስብ ቢሆንም በአመራር ላይ የነበሩትና ያሉት ወንድሞችና እህቶች በየጊዜው የሚነሱትን ችግሮች እንዳመጣጣቸው በማስተዋልና በትዕግስት እየፈቱ የቤተክርስትያኑን አድነት ጠብቀው በእግዚአብሔር ፈቃድ ከዚህ ደረጃ እንዲደርስ በማድረግ ለተከታዩ ትውልድ መልካም አርዓያ ሊሆን የሚችል ስራ አበርክ ተዋል።

## ምስጋና

በተለያዩ ጊዜዓት ከቦታችን ድረስ በመምጣት ቡራኬ በመስጠት ጊዜዓዊ ካህን እንድናገኝና ምዕመናን ለቤተክርስትያን መግዣ ገነዘብ እነድያዋጡ በማበረታታትና ቅዱስ ወንጌል በማስተማር ለረዱን አባታችን አቡነ መልከጼዴቅ።

ቡራኬ በመስጠት ለአባቶች የምነኩስናና የቅስና እንዲሁም የዲቁና ማዕረግ በመስጠት የነበረውን ችግር አቃለውልን ለነበሩት አባታችን ለአቡነ ይስሐቅ።

የፃድቁን አባታችን የቅዱስ ተክለሃይማኖትን በዓሎች በምናከብርበት ጊዜ በመገኘት ቡራኬ በመስጠትና ቅዳሴ ወንጌልን በማስተማር እንዲሁም አባታችን አባ ገብረ እግዚአብሔር በሞት በተለዩን ጊዜ በመካከላችን በመገኘት ለአፅናኑን አባታችን ለአቡነ ኤልያስ።

የቅዱስ ተክለሃይማኖትን በዓል በምናከብርበት ጊዜ በመገኘት ቡራኬ ለሰጡንና ቅዱስ ወንጌል ለአስተማሩን ለአቡነ ጉርጉርዮስ።

በአገራችን ኢትዮጵያ በደረሰው የተፈጥሮ አደጋ ለተጎዱት ወገኖቻችን እርዳታ እንድናሰባስብና በፀሎት እንድናስባቸው ለአስተማሩንና ለባረኩን አባታችን ለአቡነ ዜና ማርቆስ።

ለተከበሩ አባቶቻችን እድሜና ጤና እንዲሰጥልን እየተመኘን በጻድቁ አባታችን በአቡነ ተክለሃይማኖት ስም ልባዊ ምስጋናችንን እናቀርባለን።

### የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ መንበረ ብርሃን ቅድስት ማርያም ካቴድራል ቶሮንቶ

የቶሮንቶ መንበረ ብርሃን ቅድስት ማርያም ካቴድራል አስተዳዳሪ ሊቀ ካህናት ምሳሌ እንግዳ፣ካህናት፣መዘምራን ፣ሰበካ ጉባዔና ምዕመናን ከቦታችን ድረስ በመምጣት ቅዳሴ በመቀደስ ሕፃናትን በማጥመቅ ምዕመናን በማስተማርና በማበረታታት መዘምራን በመዘመር በችግራችን ሁሉ በመገኘት ለተክርስትያናችን ሕንፃ መግዣ ገንዘብ በማዋጣት በጊዜያዊነትም ሆነ በቋሚነት ካህናትን በማስመጣት ባጠቃላይ እራሳችንን እንድንችል ለተደረገልን ክርስትያናዊ መልካም ትብብር ሁሉ በቅዱስ ተክለ ሃይማኖት ስም ልባዊ ምስጋናችንን እናቀርባለን።

## ሞንትርያል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ መድሐኒአለም ቤተክርስትያን

የሞንትርያል መድሐኒአለም ሰበካ ጉባዔና መዘምራን ቤተክርስትያናቸውን ከመሰረቱበት ዕለት እስካሁንድረስ አቅማችው በፈቀደው መንገድ ቤተክርስትያናችንን ለማሳደግ ድራማ በማዘጋጀት ድራማውን ለምዕመናን በማሳየት ገንዘብ በማሰባሰብ እንዲሁም ለቤተክርስትያናችን ሕንፃ መግዣ ገንዘብ በማዋጣትና የችግራችን ተካፋይ በመሆን ለአደረጉልን ክርስትያናዊ ትብብር በመድሐኒአለም ስምልባዊ መስጋናችንን እናቀርባለን ።

በሚያዚያ ፲፮ ቀን ፲፱፻፹፭ ዓ.ም ቤተ ክርስትያናችን ከተመሰረተ ጀምሮ የራሳችን ሕንፃ ቤተክርስትያን እስክንገዛበት ዕለት ድረስ የተጓዝንባቸው ቦታዎች

- ሚያዝያ ፳ ቀን ፲፱፻፹፭ ዓ.ም
  በአቶ አቻምየለህ ገሠሠ ቤት
- ሚያዝያ ፲፮ እና ሚያዝያ ፳፫ ፲፱፻፹፭ ዓ.ም
  በአቶ ሞገስ ዋሴ ቤት ኦታዋ
- ሚያዝያ ፴ እና ግንቦት ፳ ፲፱፻፹፭ ዓ.ም
  በኢትዮጵያውያን ማህበር ጽ/ቤት
- ከግንቦት ፲፪ ቀን ፲፱፻፹፭ - ፲፱፻፹፰ ዓ.ም
  ሴንት አንድሪው ፕረስበትርያን ቤተክርስትያን 82 ኬንት ስትሪት ኦታዋ
- ከመስከረም ፲፱፻፹፰ - ግንቦት ፲፱፻፹፱ ዓ.ም
  ሴንት ጆን ባፕቲስት ቤተክርስትያን 96 ኤምፕረስ አቨኒው ኦታዋ
- ከሰኔ ፲፱፻፹፱ -ነሐሴ ፲፱፻፹፱ ዓ.ም
  ሴንት ዲአርክ ቤተክርስትያን 461 ኤቨረድ ሮድ ኦታዋ
- ከመስከረም ፲፱፻፹፱ - ግንቦት ፲፱፻፺፫ ዓ.ም
  ሴንት ጆን ባፕቲስት ቤተክርስትያን 96 ኤምፕረስ አቨኒው ኦታዋ
- ሰኔ ፲፱፻፺፫ - ግንቦት ፲፪ ፲፱፻፺፭ ዓ.ም
  ዶሚንየን ቻልመረስ ዩናይትድ ቤተክርስትያን 355 ኩፐር ስትሪት ኦታዋ
- ግንቦት ፲፱፻፺፭ - መስከረም ፳፯ ፲፱፻፺፯ ዓ.ም
  ሴንት ማርክ ዩናይትድ ቤተክርስትያን 142 ሊዊስ ስትሪት ኦታዋ
- መስከረም ፴ ፲፱፻፺፯ ዓ.ም
  ቅዱስ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስትያን 915 ሜርቬል ሮድ ኦታዋ

## አቻምየለህ ገሠሠ

### "ለሚያምን ሁሉ ይቻላል "ማርቆስ 9:23

የገዳሙ አበምነት ረድአቸውን ውሃ እንዲቀዳ ያዙታል ። ረድኡም የአባቱን ትዕዛዝ ተቀብሎ ብዙ ሰዓታት ወደሚያስኬደው ሥፍራ ይጓዛል ። ከቦታው ሲደርስ ግን ውሃ መቅጃውን እንጂ ከጥልቁ ጉድጓድ ጎትቶ የሚያወጣበትን ገመድ አለመያዙን ይረዳል ። ወደ ኋላው ለመመለስ አይቻልም ውሃ ሳይዝ ወደ አባቱ አይቀርብምና ።በዚያም ስፍራ ሊጠራው የሚችለው ነገር ቢኖር አምላኩን ብቻ በመሆኑ ወደ አምላኩ ፀሎት አደረገ።ፀሎቱንም ሲፈፅም በፍፁም እምነት ድምፁን ከፍ አድርጎ "አንቺ ውሃ መቅጃ ሆይ አባቴ ውሃ ሞልቼሽ እንድመጣ አዞኛል !! " ማለት ጀመረ ። ወድያውም ብዙ ሜትሮች ጥልቀት ርቆ የተቀመጠው ውሃ በማዕበል እንደተመታ ውቅያኖስ እንደ ዘንዶ እየተም ዘገዘገ የውሃ መያዣዋን ሞላት። ትዕዛዙንም ከፈፀመ በኋላ ወደ ስፍራው ተመለሰ።

ረድኡም የለመነውን ከተሳካ በኋላ አምላክን እያመሰገነ በደስታ ተመለሰ። መድኋኒታችን እየሱስ ክርስቶስ " ለሚያምን ሁሉ ይቻላል " እንዳለ ሃይማኖት ያለው ሰው የሚቸግረውም ሆነ የሚፈራው አንዳች ነገር የለውም ማርቆስ 23 ። ችግሩ ሁሉበእምነት እንደሚቃለልለት ያውቃልና ። አባቶቻችን "...በእምነት የአንበሶችን አፍ ዘጉ ፣ የእሳትን ሃይል አጠፉ፣ ከሰይፍ አፍ አመለጡ፣ከድካማቸው በረቱ..." ዛሬም ቢሆን እምነት ኋይል አለው ።ብናምን ወደ አምላካችን ብናሳስብ የማይፈፀም አንዳች ነገር አይኖርም።ምክንያቱም " ለሚያምን ሁሉ ይቻላል " ተብሏልና ። ዛሬ ተባርኮ ታቦተ ሕጉ የገባበት ቤተክርስትያንም የተገዛው በሃይማኖትና በፀሎት ፍሬ ነው።

**አባ ኃይለ ገብረኤል**